ጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት (ጎልኅድ) ሰሜን አሜሪካ
Gondar Development & Cooperation Organization (GDCO) North America
P. O. Box 53336 Washington, DC. 20009

ቀን 02/26/09

ለተከበራችሁ የጎልኅድ አባላትና ደጋፊዎች

የ2000 ዓ. ም. (2007/08) ጎልኅድ ስኮላርሽፕ ፕሮግራም አፈጻጸም ሪፖርት ይመለከታል።

በመጀመሪያ የአክብሮት ሰላምታ እናቀርባለን።

ጎልኅድ በየዓመቱ በትምሕርት ብልጫ ውጤት ላመጡና፥ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውን የመሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አወዳድሮ በመምረጥ፥ መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ሲሰጥ 13 ዓመት ሆኖአል። እንደተለመደው ያለፈውን ዓመት (2000 ዓ. ም.) ስኮላርሽፕ ፕሮግራም አፈጻጸም 20 ገጽ ሪፖርት ከአባሪዎች ጋር እየላክን፥ የዚህን ዓመት የገንዘብ አስተዋጽኦ እንድትልኩልን ዕርዳታውን በሚያገኙት ተማሪዎች ስም እንጠይቃለን።

የተለመደው ትብብራችሁና ድጋፋችሁ እንደማይለየን እንተማመናለን።

ከሰላምታ ጋር

*Eyasu Damtew*

እያሱ ዳምጠው
የጎልኅድ ዋና ጸሐፊ
ሰሜን አሜሪካ

## የ2000 ዓ. ም. የስኮላርሽፕ ፕሮግራም ሥራ አፈጻጸም ሪፖርት

ሪፖርቱ የሚያጠቃልለው በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የአንድ የትምሕረት ዘመን ተከትሎ የተከናወነውን ይሆናል። ማለት በ2000 ዓ. ም. (2007/08) የተከናወነውን ፕሮግራምና ውጤት እሚያመለክት ነው።

1. **የፕሮግራሙ ዓላማ፦**

    1.1. በጎንደር ክፍለ ሀገር በሚገኙ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች (10ኛ-12ኛ) ትምሕርት ከሚከታተሉት ተማሪዎች መካከል፤ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ትምሕርት ለመከታተል ያዳገታቸውን አወዳድሮ በመምረጥ፥ ለተወሰኑ ተማሪዎች መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት በትምሕርታቸው እንዲበረታቱና ከፍተኛ ውጤት (ነጥብ) በማምጣት ከፍተኛ ትምሕርት (ዩኒቨርስቲ) እንዲከታተሉ ለመርዳት፥
    1.2. ሴት ተማሪዎች በመሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተግተው ትምሕርት እንዲከታተሉ ለማበረታታትና ወደ ከፍተኛ ትምሕርት (ዩኒቨርስቲ) እንዲሸጋገሩ ለማስቻል፥
    1.3. ስኮላርሽፕ ያገኙ ተማሪዎች ለትምሕርት ያላቸውን ፍላጎትና ጥረት እንዲሁም በሚያመጡት የላቀ ውጤት ለሌሎች 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አርአያነት ስላለው፤ ለትምሕርት አሰጣጥ ሂደት መሻሻል አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል።

2. **እስከአሁን ምን ውጤት ተገኘ?**

የጎልጎድ ስኮላርሽፕ ፕሮግራም የተጀመረው በ1988 ዓ. ም. (1996) ነው። እስከ 2000 ዓ. ም. (2007/08) መጨረሻ ድረስ 1250 ያህል ተማሪዎችን የገንዘብ ድጋፍ ተሰጥቷል።

በ2000 ዓ. ም. የትምሕርት ዘመን በ12 መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለ300 ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ ተሰጥቷል። ለወንድ ተማሪዎች ለእያንዳንዳቸው በወር ብር 100.00 ፤ ለሴት ተማሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 120.00 ተከፍሎአል። በዓመቱ በጠቅላላው $30,000.00 ዶላር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ለጎንደር ልማት ማኅበር (ጎልማ) ጽ/ቤት ተልኮ፥ ለተማሪዎች ተከፋፍሎአል። የስኮላርሽፕ ተማሪዎች ፎቶግራፍ በየት/ቤታቸው አባሪ ሆኖአል። (አባሪ 1)

ከ300 ስኮላርሽፕ ተማሪዎች 99% የሚሆኑት ዩኒቨርስቲ ለመግባት የሚያስችላቸውን ከፍተኛ ውጤት (ነጥብ) አግኝተው እንዳለፉ ከዞን ትምሕርት መምሪያ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል።

የጎልጎድ ስኮላርሽፕ ተማሪዎች ባለፉት ዓመታትም ቢሆን የላቀ ውጤት እያገኙ ዩኒቨርስቲ ገብተው ትምሕርት መከታተላቸው ይታወቃል።

ለማስረጃ ያህል የጎልጎድ ሥራ አመራር ቦርድ ድሬክተር አቶ ወንድአየሁ ካሣ በግል ጉዳይ ጎንደር ሄደው በነበረበት ወቅት ዐቅም በፈቀደ ክትትል አድርገው አንዳንድ መረጃዎችን አቅርበዋል።

2.1. <u>በጎንደር ዩኒቨርስቲ</u> 58 ያህል የቀድሞ የጎልጎድ ስኮላርሽፕ ያገኙ የነበሩና፥ በአሁኑ ወቅት በዩኒቨርስቲው ልዩ ልዩ ኮሌጅና ፋክልቲዎች በመማር ላይ እሚገኙ፥
- 2.1.1. 45ቱ ጤና ነክ ሙያ - 2ቱ ሴቶች ናቸው። 14ቱ ሕክምና (Medicine)፥ 9ኙ ፋርማሲ (Pharmacy) 22 ጤና ሳይንስ (ጤና መኮንን) ይከታተላሉ ።
- 2.1.2. 2ቱ ሕግ (Law)፥ 3ቱ ቱሪዝም (Tourism)፥ 7ቱ በሌሎች (Business, Statistics, Applied Math's, Psychology) ይከታተላሉ።
- 2.1.3. <u>ወርቅነህ አስማረ</u> (አዲስ ዘመን 1996 ዓ. ም. ስኮላርሽፕ)፥ ጎንደር ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቶ፥ በአሁኑ ወቅት ኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት መምሕር (Lecturer) ነው።

2.1.4. መኩ ደጉ ተሾመ (ማክሰኞት - 1999 ዓ. ም. ስኮላርሽፕ) ለዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተና አጠቃላይ ከፍተኛ ነጥብ 500 ነው። መኩ 417 ነጥብ በማምጣት አማራ እሚባለው ክልል ከተፈተኑት ጠቅላላ ተማሪዎች 2ኛ ደረጃ አግኝቷል። እስከዛሬ ጎንደር ክፍለ ሀገር የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት 319 ነበር። መኩ በዚህ ዓመት ጎንደር ዩኒቨርስቲ በሕግ ትምህርት 2ኛ ዓመት ተማሪ ነው።

2.2. አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፥ ተስፋዬ ውቡ ኃይሉ (ከእስቴ - 1998 ዓ. ም. ስኮላርሽፕ) ኢኮኖሚክስ፤ ማረው አበበ (ወረታ - 1999 ዓ. ም. ስኮላርሽፕ) ጋዜጠኛነት (School of Journalism) ከፍተኛ ትምሕርት በመከታተል ላይ ይገኛሉ።

3. ያጋጠሙ ችግሮች፥

3.1. ዋናው ለተማሪዎች እሚከፈለው ገንዘብ በጊዜው አለመገኘቱ ነው። በ2000 ዓ. ም. የትምሕርት ዘመን ወጭ ከሆነው ብር ውስጥ 50% ገቢ የተገኘው እዚሁ ዩናይትድ ስቴትስ ከአንድ በጎ አድራጊ ድርጅት ነው።

የጎልጎድ አባላትና ደጋፊዎች ለዚህ የልማት ፕሮግራም ያላቸው አመለካከትና ድጋፍ ቀና ቢሆንም፥ በገንዘብ ዕርዳታ በኩል ጎልቶ አይታይም። ለምሳሌ በ2007/08 ከ46 አባላትና ደጋፊዎች የተገኘው ገቢ $8,100.00 ብቻ ነበር። (አባሪ 2) ለ2000 ዓ. ም. (2007/08) የትምሕርት ዘመን ከተላከው ገንዘብ $14,400.00 ዶላር ከዲሲው የጎንደር ልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት ድርጅት (ጎልማአድ - የጎልጎድ ዲሲ ቻፕተር) በብድር ባይገኝ ኑሮ ስኮላርሽፕ ፕሮግራም ሊቋረጥ ይችል እንደነበረ ይታወሳል። $100.00 ዶላር እዚህ ሀገር የ16 እስር እንጀራ ዋጋ ነው። ሀገር ቤት ለ1 ስኮላርሽፕ ተማሪ ለ10 ወር (1 ዓመት) ክፍያ የሚሸፍን ነው። ወይንም $1,000.00 ዶላር ለ10 ተማሪዎች የአንድ ዓመት ክፍያ ሊሸፍን ይችላል። (አባሪ 2)

3.2. በያዝነው ዓመት (2001 ዓ. ም.) የስኮላርሽፕ ተማሪዎችን አወዳድሮ ለመምረጥ የሚረዳ የተሻሻለ መመሪያ ለጎልማ ተላልፎ በሥራ ላይ ውሎአል። በ21 መሰናዶ ት/ቤቶች 300 የስኮላርሽፕ ተማሪዎች ተመርጠው ትምሕርታቸውን በትጋት በመከታተል ላይ ናቸው።

3.3. ጎንደር ከተማ በሚገኘው የጎልማ ጽ/ቤት የተከሰቱ የአስተዳደር ችግሮች፤ ከጎልማ ቦርድ አባላት ጋር በመነጋገር መፍትሔ እንዲያገኙ ተደርጎአል።

4. ማጠቃለያ፥

የጎልጎድ ስኮላርሽፕ አነስተኛ ድጋፍ በማጣት ሊሰናከል የነበረውን የወጣቶች ሕይወት ለመታደግ ችሎአል። "ጋን በጠጠር ይደገፋል እንዲሉ።" በዚህም ምክንያት ይህ የልማት ፕሮግራም በመሰናዶ ት/ቤቶች ድሬክተሮችና መምሕራን፥ በተማሪዎች፥ በወላጆች፥ በትምሕርት ባለሙያዎች፥ በጎልማ ቦርድ አባላትና ደጋፊዎች ከፍተኛ ድጋፍ የተሰጠውና ዕርዳታ ለሰጡትም ምስጋናና ክብርን ያተረፈ ስለሆነ፥ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ታምኖበታል።

ከብዙ በጥቂቱ ቀደም ሲል ስኮላርሽፕ ያገኙ ከነበሩት ተማሪዎች፥ በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርስቲ ከፍተኛ ትምሕርት ከሚከታተሉት የሁለቱን እንጠቅሳለን።

4.1. አይንሸት አዳነ ይባላል። ጎንደር ዩኒቨርስቲ 4ኛ ዓመት ሕክምና (Medicine) ተማሪ ነው። ሁለተኛ ደረጃ የተከታተለው ትክል ድንጋይ (ልማት በር) እና ፋሲለደስ (ጎንደር) ነው።

"ማኅበሩ (ጎልጎድ) ላደረገልኝ ዕርዳታና ማበረታቻ እጅግ አመሰግናለሁ። እኛም ከፍተኛ ኩራት ተሰምቶናል። … ለአሜሪካ ያሉትን የአካባቢው ተወላጆች ቀስቅሳችሁ ለእኛ አርአያ እንድትሆኑ እንፈልጋለን።"

4.2. <u>ደሴ አበባው አንጋው</u> ይባላል። ጎንደር ዩኒቨርስቲ በሕክምና ኮሌጅ ለጤና መኮንነት (Health Officer) 2ኛ ዓመት ተማሪ ነው። ከነፋስ መውጫ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ነው የመጣው።

"ጎልማ (ጎልጎድ) በመሰናዶ ት/ቤት ያደረገልኝ ድጋፍ እኛ ተማሪዎች ጉብዝናችን እንድናጠናክር የሞራል ድጋፍ ከማድረጉም በላይ ችግራችንን ለማቃለል፣ በትምሕርታችን ላይ ተፅዕኖ እንዳይደርስብን ታላቅ እገዛ አድርጎልናል። ስለዚህ አሁንም ቢሆን ይህን ስራውን አጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል።"

4.3. <u>ትዕግሥት ኃይሉ</u> ትባላለች። ጎንደር ዩኒቨርስቲ 4ኛ ዓመት ሕክምና (Medicine) ተማሪ ናት። ከአዘዞ (ጎንደር) 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የነበረች።

"ከጎልማ (ጎልጎድ) ለ2 ዓመታት ዕርዳታ አግኝቻለሁ። … መጀመሪያ ትልቅ ነገር የሞራል ዕርዳታ ነው። … እኛን አስባችሁ ለሀገራችን ትልቅ ፍቅር እንዲኖር አድርጋችሁ ስላሰባችሁንና እኛም ወደፊት ስለወገናችን እንድናስብ ስላደረጋችሁን በጣም እናመሰግናለን።"

4.4. በ2000 ዓ. ም. በጎንደር ዩኒቨርስቲና በመሰናዶ ት/ቤቶች ትምሕርት በመከታተል ላይ ያሉትን ተማሪዎች የሚያሳይ ፎቶግራፍ አባሪ ሆኖአል። (አባሪ 3)

ፌብሪዋሪ 2009